## GRD AT ITS CURRENT STAGE

### This is progress






# ህዳሴ  እኮ ህዳሴ ነው!

ድሕነትን በቃኝ ብሎ ጨክኖ ካመረረ፤
ተስፋን ስንቅ አርጎ ይዞ ጉዞውን ከጀመረ፤
ህዝብም  ሆነ ግለስብ መሻሻሉ የማይቀር ነው፤
መሸነፍን ምርጫ  ብሎ መደራደር ካላማረው።

የአገሬም ህዝብ እንደዚሁ ከመረረው እበት መዛቅ፤
ከሰለቸው ኩበት መሞቅ፤
አሻፈረኝ ብሎ ይነሳ፤
ህዳሴን ስንቅ አድርጎ፤ ህዳሴን ተስፋ አድርጎ
በድህነት ላይ ጦር ያንሳ።
ይኸ ህዝብ እኮ በቃኝ ማለት አለበት
በላሊበላ ብቻ ኮርቶ፤ በአክሱም ሐውልት መንጠራራት።

እስከመቸስ ነጠላ ለብሶ በአድዋ ድሉ ደረት ይንፋ፤
ታሪክ ላይ ታሪክ ደርቦ ድሕነትን ሳያጠፋ?
እስከመቸስ በፋሲል ግንብ ተደብቆ ይቀመጣል፤
እስከመቸስ ስልጣኔን ታሪኬ ብሎ ይጀነናል?

እስከመቸስ ለምኖ፤ እጅ ዘርግቶ ይኑር
እስከመቸስ መብራት አጥቶ    ፋንድያ አዳፍኖ ይደር?

እስከመቸስ ይጨቃጨቅ
እስከመቸስ ይቦጫጨቅ
እስከመቸስ አንገት ደፍቶ ለድሕነት ቦታ ይልቀቅ?

ይኽ ሕዝብ እኮ በቃኝ ማለት አለበት፤
በቃኝንም በቃኝ ብሎ
በቃኝ ብሎ ለመነሳት።
ለዚህ እኮ ነው ህዳሴ
ህዳሴ ነው የሚባለው፤
አዲስ መእራፍ እንዲከፈት፤ ሕዝቡ ተስፋ እንዲኖረው።
ይኽ ድምፅ እኮ ነው እኔን ከውስጤ የቀሰቀሰኝ፤
ሕሊናዬን አስጨንቆ
ለልቤ ልብ ሰጥቶ
እጄን ብዕር አሲዞ
ምላሴን ጎልጉሎ አውጥቶ
ህዳሴ እኮ ህዳሴ ነው ብዬ እንድናገር ያረገኝ።
ህዳሴ እኮ ህዳሴ ነው!

ሽመልስ አማረ
ቴምፕል ሲቲ፤  ካሊፎርኒያ
1/15/2012